# “ከህዝባችን ጋር ሆነን የማናልፈው ችግር የለም!”

*አጩሌ (ከአሜሪካ ግቢ) 03-31-18*

አዲሱ የኢህአዴግ ሊቀመንበር ፓርቲውን በመምራትና ኢህአዴግ ረጅም ጊዜ ወስዶ ውስጡን በመፈተሽ የለያቸውን ችግሮች እንዲሁም የሪፎርም ሂደቶች ወደ ስኬት በመቀየር የሚኖራቸው ሚና ከፍተኛ መሆኑ እንደተጠበቀ ሆኖ ሊቀመንበሩን ከኢህአዴግ ውጭ ማሰብ ከንቱና የዋህነት ነው።

በሌላ አነጋገር የግንባሩን ሊቀመንበር የፈጠረው ኢህአዴግ ራሱ መሆኑን አለማሰብ ስለ ኢህአዴግ አለማወቅ ነው። ይልቁንም ሊቀመንበሩን ለይቶ በማጉላት ኢህአዴግን የማኮሰስና የማሳነስ አጀንዳ ተመራጩን ሊቀመንበር በመደገፍ ሳይሆን በኢህአዴግና አመራሩ ላይ ጥርጣሬ ከመፍጠር ጥልቅ ፍላጎት የሚነሳ ነው።

ድርጅቱ እንደገለፀው ተመራጩ ሊቀመንበር በግንባሩ ማዕከላዊ ኮሚቴ በተደረገ ዴሞክራሲያዊ ውይይት ግንባሩን የመምራት ብቃታቸው በመታመኑ የኢህአዴግ ሊቀመንበር እንዲሆኑ ተመርጠዋል። ህዝቡ በኢህአዴግ ረጅም የውይይት ጊዜያት በተለያየ መልኩ ሲነሱ የነበሩ ሃሳቦችንና እንደ አገር ሲስተዋሉ የነበሩ ያፈጠጡ ችግሮችን ወደ መፍትሄ በመቀየር እንደ አገር ያጠላው ስጋት በየትኛው የኢህአዴግ አመራር ወደተሻለ አጋጣሚ ይለወጥ ይሆን እያለ ሲጠብቅ መቆየቱም የሚታወቅ ነው።

ኢህአዴግ አዲሱን ሊቀመንበር ከመረጠ በኋላም ህዝቡ በግንባሩ ዴሞክራሲያዊ ውይይት የተመረጠውንና የድርጅቱንና የአገሪቱን ቀጣይ እጣ ፈንታ የተሻለ ለማድረግ አቅም አለው ባለው መሪ ላይ እምነቱን ከማሳደር በላይ አብሮ ለመስራት ዝግጁነቱን በመግለፅ ላይ ይገኛል።

ከዚህ በተቃራኒ ይህን በሁሉም የአገሪቱ አቅጣጫ እየተገለፀ ያለውን ህዝባዊ በጎ መነሳሳት መቀልበስ አዳጋች የሆነባቸው፣ ከህዝቡ ሲነሱ የነበሩ ቅሬታዎችን ተጠቅመው ህዝባዊ ስርዓቱን በሀይል ለመጣል ሞክረው ያልተሳካላቸውና በተለይ የህዝቡንና የአገሪቷን ሰላም አስተማማኝ ለማድረግ የተሻለ እድል የፈጠረው የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ ያልተመቻቸው ወገኖች ኢህአዴግንና ሊቀመንበሩን ነጣጥሎ ለማሳየትና ለመከፋፈል መሯሯጥ ጀምረዋል።

ሲሻቸው ኢህአዴግን ከመሰረቱት ድርጅቶች ኦህዴድ የግንባሩ አባል መሆኑን ዘንግተው የድርጅት ጥርጣሬን ለማንገስ፣ ምርጫው በምክር ቤቱ አባላት የግል የመወሰን ኃላፊነት በሚስጥር የተካሄደና ማን

ለማን ድምፅ እንደሰጠ በማይታወቅበት ሁኔታ አንዱ ፓርቲ አንዱን ደግፎ ሌላውን ድምፅ እንደነፈገው አድርገው አሉባልታ በማዛባት በሌሉበት ብዥታን ለመፍጠር ሲዳክሩም ተስተውለዋል።

ይህ መበተንና መፈራረስን ለማስከተል ተለዋዋጭ የሆነና በኢህአዴግ መካከል ጥርጣሬ የመፍጠር የሁልጊዜ አግላይ ስልታቸው ማረፊያ ስላጣም ከወዲሁ ተስፋ ቆርጠው ተስፋ ቆራጭነትን ለማንገስ በረጅም ሙከራ ውስጥ ተጠምደው ተስተውለዋል። ባለ በሌለ አቅማቸው በቀቢፀ ተስፋ የየግል ፍላጎታቸውን በማይወከሉበት ግንባርና ድርጅት ላይ ለመጫን ሲዳክሩም ታይተዋል።

ቀድሞ ነገር የመስመር ልዩነታቸውን ዘንግተውና በኢህአዴግ ውስጥ የሚመኙት ምን እንደሆነ በግልፅ ለራሳቸው ሳይገባቸው፣ ኢህአዴግ ራሱን ፈትሾና በጥልቅ ገምግሞ እተገብራቸዋለሁ ብሎ ቀን የቆረጠላቸውን ጉዳዮች በመንጠቅ መልሰው አጀንዳ ሰጪ ሆነውም ተስተውለዋል።

የኢህአዴግ አጀንዳዎች ከሊቀመንበሩ እስከ ታችኛው አባል በአንድ ሰንሰለትና በጥብቅ ዲሲፕሊንና በመስመር ፅናት ላይ ተመስርተው የሚተገበሩ መሆኑን ያልተረዱት እነዚህ ወገኖች፣ ቢያንስ ኢህአዴግ ከገመገመው የስልጣን አተያይ ችግር ጉዳይ እንኳ መማር አለመቻላቸውን እያረጋገጡልን ነው።

የተመራጩ ሊቀመንበር ወንበር የድርጅቱና መንግስት የሚመራበት ፕሮግራም ማስፈፀሚያ መሆኑን ዘንግተው ሲሻቸው ኢህአዴግ የሚመራው መንግስት ለራሱ ለኢህአዴግ መሰናክል ይሆንበታል፤ አንዳንዴም እነሱ በሩቅ ሆነው የሚጠሏቸውን ሰዎች ማስወገጃ ሊሆን ይገባል እያሉ ለማምታታት ሲሞክሩ ይስተዋላል።

እነዚህ ወገኖች ቢያንስ ኢህአዴግ በትንሹ ላለፉት 2 እና 3 ወራት እንደ ብሄራዊ ድርጅትና እንደ ግንባር ራሱን በጥልቅ በማየት "የኢህአዴግ ስልጣን ህዝቡ የመረጠው ፓርቲ ስልጣን ነው፣ ግንባሩ የያዘው የመንግስት ስልጣንም የመረጠውም፣ ያልመረጠውም ህዝብ ስልጣን ነው" ብሎ ከገለፀው በጥቂቱ እንኳ እስካሁን መማር አልቻሉም።

ሌላው ቀርቶ ጠቅላይ ሚኒስትር ኃይለማርያም ደሳለኝ ስልጣን የህዝብ መሆኑን ካሳዩበት አስተማሪ የሽግግር ሂደት ቅንጣት ነገር ማየት አልቻሉም። ለዚህም ነው የእነዚህ ወገኖች ግብ ከህዝቡ ጥያቄና በጥያቄው ማግስት ከተመለሰው ምላሽ ጋር ፈፅሞ ዝምድና የሌለው። ይልቁንም ፍላጎታቸው ስርዓትን

በሀይል መቀየር ላይ የታጠረ በመሆኑ አጀንዳቸው ተለዋዋጭና የግንባሩን ሊቀመንበርና ኢህአዴግን ነጣጥሎ ማየት ላይ ያተኮረው።

ለእነዚህ ወገኖች የአዲሱ ሊቀመንበር ምርጫ፣ የኢህአዴግ ውስጠ ድርጅት ትግል ስኬትና ህዝቡ መንግስትን በሚመራው ድርጅት መንግስታዊ አፈፃፀም ላይ ባለው እርካታ ማጣት ጉዳይ ግንባሩ በጥልቅ ተወያይቶ መፍትሄ ላይ የደረሰበት ውጤት ሆኖ አይታያቸውም። የግንባሩ ሊቀመንበር የአራቱ ብሄራዊ ድርጅቶች የጋራ ግንባር ሊቀመንበር ሆኖም አይገፅላቸውም።

ኢህአዴግ ራሱን ለረጅም ጊዜያት በጥልቅ ሲፈትሽ በአገሪቱ የተለያዩ አካባቢዎች ህዝቡ እንዲጠቀም ለማድረግ እልህ አስጨራሽ በሆነ ሁኔታና በጥሩ አፈፃፀም የደረሰባቸውን ስኬቶች፣ ህዝቡ ካልረካባቸውና ቅሬታውን በስፋት ከሚያነሳባቸው ጉዳዮች ጋር አነፃፅሮ ገምግሟል። በአገራችን ባለፉት ዓመታት እጅግ አመርቂ ስኬቶች እንደተመዘገቡ ሁሉ ህዝቡን የሚያማርሩ በተለይም ከስልጣን አተያይ ጋር የተያያዙ ስር የሰደዱ የመልካም አስተዳደር ችግሮች እጅግ በርካታ እንደነበሩ በተገቢው አይቷል።

ኢህአዴግ በሚመራቸውም ሆነ አጋር ድርጅቶች በሚያስተዳድሯቸው ክልሎች፣ ህዝቡ ራስን በራስ በማስተዳደር መብቱ ተጠቅሞ ከራሱ ውስጥ አውጥቶ የመረጣቸው በየደረጃው ያሉ መሪዎች በህዝብ አይን ምን እንደሚመስሉም በበቂ መጠን ተገንዝቧል። ለህዝብ ጥቅም ከማሰብ ባልሆነ የግል መቀመጫንና የግል ኪራይን ለማቆየትና ለመሸፈን ሲባል የተፈጠረው ያልተገባ መጠራጠር በህዝባችን ላይ ያስከተለው ጉዳት ዘግናኝ መሆኑንም ኢህአዴግና አራቱ ብሄራዊ ድርጅቶች በቁጭት ገምግመዋል። በዚያው መጠን የማስተካከያ እርምጃ መውሰድ ጀምረዋል።

ይህን የግንባሩን አካሄድ የሰላም፣ የልማትና የዴሞክራሲው ጉዳይ በተጨባጭ የሚያሳስባቸው የሁሉም ክልሎች ህዝቦችና ኃላፊነት የሚሰማቸው የየትኛውም ፖለቲካ ድርጅት አመራሮች እንዲሁም የሲቪክ ማህበረሰብ አባላት ከማድነቅ ባለፈ፣ ኢህአዴግ የጀመረውን ሪፎርም በጀመረው ብስለት የተሞላበት አካሄድ እንዲቀጥለው እየመከሩ ነው። ከኢህአዴግ ጋር በመሆንም ለመስራት ዝግጁነታቸውን እያረጋገጡ ነው።

በአንፃሩ የጥርጣሬው መፅዳትና የህዝቡ አብሮነትና እፎይታ ጥቅማችንን ይነካል ብለው የሚያስቡ በየትኛውም ደረጃና አሰላለፍ ውስጥ ያሉ ሀይሎች በኪራይ አስተሳሰቡና በቅሬታው ውስጥ ከፍታቸውና ጥቅማቸው እንዳይነካ በመፋጠጥ ውስጥ እንድንኖር ይሻሉ። በዚህም ምክንያት እያንዳንዷን የኢህአዴግ

ርምጃ በመሰንጠቅ፣ ግርታ በመፍጠር፣ ጥርጣሬ እንዲያይል በማድረግ ወዘተ… ፍላጎታቸውን ለማራመድ ይሻሉ።

በእርግጥ ህዝቡ አሁን ሁሉም ነገር ግልፅ እየሆነለትና ራሱም ለሰላሙ፣ ለልማቱና ለዴሞክራሲው መሻሻል የበለጠ እየተነሳሳ ስለመጣ፣ ኢህአዴግ ይህን የኪራይ አስተሳሰብ በውስጡም ሆነ በውጭ ለመታገል የተመቸ አውድ ፈጥሯል፤ ተፈጥሮለታልም።

ኢህአዴግ ከነጉድለቱ በዚህች አገር ህዝቦች በእኩልነት የሚኖሩበት ስርዓት እንዲፈጠር፣ ይህን እድልም ለጋራ ልማት፣ ፍትህ፣ ሰላምና እድገት በማዋል ህዝባችን ከጊዜ ወደ ጊዜ የተሻለ ህይወት እንዲኖር ማድረጉ ሊዘነጋ አይችልም። ይህን ሀቅ በጭፍን ማጥላላትና እንዳልነበረ መቁጠርም ማንንም አያሳምንም። ግንባሩ እነዚህን ስራዎች ያለ ህዝቡ ተሳትፎና ብቃትም አልፈፀማቸውም።

ስለሆነም ይህን የጋራ ውጤት ክደው ስርዓቱ እንዳልነበረ የሚቆጥሩም ሆኑ፣ የኢህአዴግን ራስን የማየት ጥልቀትና በየጊዜው እየታየ ያለውን የመታደስ ብቃት ከድርጅቱ ውጪ ለማንም መስጠት አይቻልም። ኢህአዴግ በረጅም የግምገማ ጊዜው የወሰናት እያንዳንዷ ውሳኔም ሆነች በመጨረሻ የደረሰበት ድምዳሜ በራሱ በኢህአዴግ እምነትና የመወሰን አቅም እንጂ በማንም ጫናና ጥምዘዛ የተፈፀመ አይደለም። በጫና ራስን አሳልፎ መስጠት የአራቱ ብሄር ድርጅቶች ግንባር የሆነው ኢህአዴግ ባህሪም አይደለም። ይህን አለመረዳት የድርጅቱን አብዮታዊ ዴሞክራሲ መስመርና የረጅም ጊዜ ልምዱን አለመረዳት ጭምር ነው።

አጀንዳቸውን በህዝቡ ላይ ለመጫን ያለ የሌለ እንቅስቃሴ ሲያደርጉ የነበሩ ወገኖች ኢህአዴግ ለውጥ አያመጣም፣ አብቅቶለታል፣ መፍትሄውም Political Surgery ነው ሲሉ እንዳልነበር ሁሉ፣ ይሄው አጀንዳቸው አገሪቱን ለመበተን ያለመው ሀይል የሰጣቸው መሆኑ ሲጋለጥና ኢህአዴግ በስተመጨረሻ የደረሰበት ድምዳሜም በሁሉም የአገሪቱ አቅጣጫ ባለው ህዝብ ሲደገፍ አቋማቸውን በሌላ የመከፋፈል ሴራ ለመቀየር ተገደዋል።

ሊቀመንበሩና ኢህአዴግ በባላንጣነት ተስለው እንዲታዩ ለማድረግ፣ የጠቅላይ ሚኒስትሩና ህገመንግስታዊ ተቋማት ግንኙነት ጉዳይ ጥርጣሬ እንዲያዝበት ለማስቻል በአገር ውስጥና በውጭ ባሉ መገናኛ ብዙሃናት ያለ የሌለ አቅማቸውን እየተጠቀሙ ነው።

እነዚህ ወገኖች ቢያንስ የሉዓላዊ ስልጣን ባለቤቶች የኢትዮጵያ ህዝቦች መሆናቸውን በግልፅ በማሳየትና የተሻለ መፈፀም የሚችል ሀይል መውጣት አለበት ብለው በቅርቡ ራሳቸውን አርአያ አድርገው ካቀረቡት ጠቅላይ ሚኒስትር ኃይለማርያም መማር አልቻሉም የሚያስብለው ለዚህም ነው።

ኢህአዴግ አዲሱን ሊቀመንበር ለህዝቡ ካሳወቀና የፊታችን ሰኞም በህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ሊቀመንበሩ የጠቅላይ ሚኒስትርነት ቃለመሃላቸውን እንደሚፈፅሙ ከገለፀ በኋላ ባወጣው ድርጅታዊ መግለጫ መቋጫ "ከህዝባችን ጋር ሆነን የማናልፈው ችግር የለም!" በማለት አለቃው ህዝቡ መሆኑን በፊትም አሳይቷል፤ አሁንም የህዝቡን እርካታ ባረጋገጠ ጅማሬ ህዝብ አለቃው መሆኑን አረጋግጧል።

በኢህአዴግ ውስጥ ጥርጣሬ ለማንገስ የሚሞክሩ በውስጥም በውጭም ያሉ የትኛውም ወገን በእርግጥም የዚህች አገር ጉዳይ ያገባናል የሚሉ ወገኖች፣ ይህን የህዝብ ፍላጎት ህዝብን በማክበርና በህዝብ መካከል ያለ ግንኙነት ላይ ጥርጣሬ ባለመፍጠር፣ ለራስ ኪራይ ሲባል ከሚፈፀም የማጠራጠርና ማጥላላት ተግባር በመቆጠብ ሊፈፅሙት ይገባል።